የጎንደር ሕብረት

gonderhibrert72@gmail.com /website: www.gonderhibret.org

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለወያኔ ሞት፤ ለሕዝባችን የትግል ግለት!

ይድረስ ለጎንደር ሕዝብ ቁ. 14

በአንዲት አገር የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የሚታወጀው የውጭ ወራሪ የአገርን ደህንነት የሚያሰጋ ሲሆን ወይም አገር በቀል አደጋ ሲከስት ነው። ይህ አገር በቀል አደጋ የተፈጥሮ አደጋ ሊሆን ይችላል ወይንም በህዝብ ሂይዎት ላይ ከፍተኛ እልቂትና ሺብር የሚፈጥር አንድ የተደራጀ አጥፊ ኃይል ሲፈጠር ብቻ ነው።

በአሁኑ ሰዓት በአገአችን ኢትዮጵያ ከላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች ፈጽሞ የሉም፤ ማለትም የውጭ ወራሪ የአገሪቱን ደህንነት አላሰጋም። የተፈጥሮ አደጋም ይሁን በቡድን የተደራጀ ለአንድነታችን የሚያሰጋ አገር በቀል ኃይል አልተከሰተም። የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ማወጅ ያለበ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለአገራችንና ለሕዝባችን ከፍተኛ ስጋትና አደጋ ለሆነው በወያኔ መንግሥት ላይ ብቻ ነው። የአገሪቱ ህልውና መንግሥት በፈጠረው ብልሹ አስተዳደር ምክንያት እንደ አገር እንዳትቀጥል ገደል አፍፍ ላይ ያደረሳት ህዝቡ ሳይሆን በሙት መንፈስ የመግዛት ቅዠት እየተገፋ ያለው ወያኔ ነው። በአሁኑ ሰዓት የሰው ልጆች ከእንሰሳ በታች በከፋ ሁኔታ በራሳቸው መንግሥት እየተጨፈጨፉ ያሉባት አገር ኢትዮጵያ አንዷ ናት ብንል ማጋነን አይሆንም።

በጎንደር፤ በኦሮሚያ፤ በባህርዳር፤ በወልድያና በሌሎችም ከተሞች በተደረጉ ሰላማዊ ሰልፎች ላይ ሆን ብሎ በመተንኮስ ግድያ የፈጸመውና በብዙ ሽዎች የሚቆጠሩ ዜጎችን እስርቤት የከተተው ወያኔ ነው። ወያኔ ግድያውን ከመፈጸሙ በፊት በሰልፈኛው ህዝብም አንድም የሰው ንብረት አልተቃጠለም፤ እርስ በርስም ቢሆን አንድም ግጭት ሳይኖር ፍጹም ሰላማዊ በሆነ መንገድ ብሶቱን በማሰማት ላይ ነው ሰልፉ ሲካሄድ የነበረው።

ታዲይ ይህ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በዝህብ ግፊት ከገደል ጫፍ ላይ የተንጠለጠለውን የወያኔን መንግሥት ሂይዎት ለማሰንበትና ዜጎችን በነጻ እርምጃ ለመግደል፤ ያለፍርድቤት ትዛዝ በጠራራ ጸሐይ እያፈሱ ለማሰር፤ ቤትና ንብረታቸውን ለመበርበር፤ እንዲሁም አሁን ከእስር ተለቀቁ የተባሉ ጥቂት ግለሰቦችን ከህዝባቸው ጋር እንዳይገናኙ ለመቆጣጠር የታወጀ አዋጅ መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል። በዚህ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ወያኔ በውስጡ ያለውን የተወሳሰብ ችግር አስተካክሎ ለመመለስና በህዝብ ላይ ከዚህ የከፋ ስቃይ ለማድረስ የታሰበ አዋጅ ነው።

በመጀመሪያ ደረጃ ወያኔ እራሱ ያወጣውን ህግ በራሱ የሚጥስ አጉራ ዘለል ስለሆነ እንጅ ይህ አሁን የታወጀው የአስቸ ኳይ ጊዜ አዋጅ ህገወጥ ነው። በራሱ ህገመንግሥት መሰረት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ህጋዊ የሚሆነው ፓርላማው ሲያጸድቀው ብቻ ነው። ስለዚህ ሕዝባችን ሳይሆን ህግ እየጣሰ ሁከት እየፈጠር ያለው፤ ማሰብ የተሳነው የዓለም አቀፍም ሆነ የአገር አቀፍ የፖለቲካ ክስተትን እና የአምባገነኖች ፍጻሜን ማንሰላሰል ወይም ማገናዘብ የተሳነው የወያኔው ጉግ ማንጉግ ስብስብ ብቻ ነው።

<u>የተከበርከው የጎንደር ሕዝብ ሆይ!</u>

"የነብርን ጅራት አይዙም፤ ከያዙም አይለቁም" ነውና ፍርኃትን ሰብረህ ከአባቶችህ የወረስከውን ጀግንነት ተላብሰህ፤ ከአስከፊው አፋኝ ሥራዓት ለመላቀ ትግልህን አቀጣጥለህ ያቆሰልከውን የወያኔን ስርዓት ከስሩ ነቅለህ እስካልጣልክ ድርስ አንዳንድ እስረኞችን በመፍታቱ ወይም ኃይለማርያምን በሌላ አሻንጉሊት ሊተካ በመዘጋጀቱ በእውነት ለለውጥና ለተኃድሶ እየተዘጋጀ መሥሎህ ጭራሽ እንዳትዘናጋ። ወያኔ መታደስ ቀርቶ የማይታበስ ከአንድ ጎሳ የፈለቁ ግትሮች

የተሰባሰቡበት ቡድንተኛ ድርጅት ነው። በብዙ ሺዎች ከሚቆጠሩት በቃልቲና በአዋሽ እስር ቤቶች እየማቀቁ ካሉት ወገኖቻችን ጥቂቶችን በመፍታት ከዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የመጣበትን ጫና ለማስተንፈስ እንጂ፤ በቀን በቀን ሌሎችን ወገኖቻችንን ሌት በጨለማ ቀን በብርሃን እያፈነ በፈታቸው ታሳሪዎች ምትክ ወደ እስር ቤት እየወረወረ ነው።

ይልቁንም መገንዘብ ያለብን ከዚህ ቀደም የታወጀው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በሌሎች ከተሞች ተነሳ በተባለበት ጊዜ እንኳ በጎንደር ላይ የወታደር ወከባው ምን ጊዚም ቢሆን አልተቋረጠም ነበር። ስለዚህ ይህ አዲሱ አዋጅ እስከሁን ከነበረው መከራና ወታደራዊ ወከባ ግድያና እሥራት የባሰ የሚያመጠው አዲስ ነገር የለም። የባሰ የሚያደርገው ግን ወያኔ የሚለፈውን የሰላም ለውጥ ወይም ተኃድሶ ተስፋ በማድረግ ተዘናግተህ የትግል ክንድህን ካጠፍክ ነው።

እናስተውል! ትግላችን ወያኔ በየእስር ቤቱ ያነራቸውን በሺ የሚቆጠሩ ወገኖቻችንን ለማስፈታት ብቻ አልነበረም። በመሬት ጥም ምክንያት ተከዜን ተሻግሮ የጨፈጨፋቸው ወገኖቻችን ደም በየአንዳንዳችን ህሊና ውስጥ ይጮሃል። ድንበራችን ተከዜ ሕዝባችን አማራ! የሚለው መፈክራችን ገና ምላሽ አላገኘም። የዲሞክራሲያዊ ጥያቄያችን ፈጽሞ በጨረፍታ እንኳ አልተመለሰም። ከእስር የተፈቱ የሰላም ታጋዮቻችን በአግባቡ እንኳ በሰላም ከማህበረሰባቸው ጋር እንዳይገናኙ በአዋጅ የቁም እስረኛ እንዲሆኑ አድርጓል። የሰሞኑን የነ ዶ/ር መራራን የምዕራብ ኦሮምያ(ነቀምት) ጉብኝት እቀባ ማስተዋል በቂ ማሥረጃ ነው።

በአጠቃላይ ከጠባቢ እሥር ቤት የወጡም፤ በሰፊው እስር ቤት ያለው መላው ሕዝባችን ከወያኔ ለመላቀቅ የጠነከረ ትግል የሚያስፈልግበት ወቅት ላይ ነን። በተለይ ደግሞ በኢትዮጵያ መሬት በአሉ እስር ቤቶች ሁሉ በከፍተኛ ቁጥር የሚገመት ሕዝብ ያለው የጎንደር ወጣትና አዛውንት መሆኑን ከእስር ቤት ከርመው የሚወጡ ሁሉ የሚመሰክሩት ሐቅ ነው።

ስለዝህ መላው የጎንደር ሕዝብ የምታደረገውን የነጻነት ትግል ከሌሎች ኢትዮጵያዊያን ጋር በማበር ጠንክረህ መቀጠል አማራጭ የሌለው ሐቅ ነው። ሕልውናህና መብትህ የሚከበረው ወያኔ ከስልጣን ሲወገድና በአገራችን ሰላምና ዴሞክራሲ ሲሰፍን ብቻ ነው። የነጻነት አየረ የሚተነፈሰው በቆራጥ ትግል እራስን ነጻ ሲያወጡ ብቻ ነው።

በመጭረሻም፡-

የጎንደርህ ህብረት ለኢትዮጵያ አንድነት በጠባቢ እስር ቤት ለዓመታት ሲሰቃዩ የነበሩት ወገኖቻችን በሰፊው የወያኔ በረት ውስጥ ከሚሰቃየው መላ ህዝባቸው ጋር ለመገናኘት በምብቃታቸው የተሰማን ደስታ ከፍ ያለ ነው። ይሁን እንጂ አሁንም በቀጣይነት ወያኔ በህዝባችን ላይ የሚደረሰውን አፈና ግፍና መከራ እንዲሁም ሰቆቃ ሁሉ የእኛም ጭምር ስቃይ በመሆኑ አቅማችን የሚፈቅደውን ሁሉ ለማድረግ የገባነውን ቃል ዛሬም እንደገና በማደስ ከህዝባችን ጎን በመቆም ለመብቱ ለመሟገት ወደ ኋላ እንደማንል ድጋሚ ቃል እንገባለን።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!

የጎንደር ሕብረት ለኢትዮጵያ አንድነት።

02/25/2018